

# ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በጀት የቤተሰብ እና የማኅበረሰብ መመሪያ

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

GOVERNMENT OF THE
DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR



ውድ የዲሲፒኤስ ማኅበረሰብ፣

በዲስትሪክቱ በመላ የትምህርት ክፍሎችን በምጎበኝበት ጊዜ፣ አስደሳች የትምህርት ገጠመኘኞች፣ የሚፈጥሩ የትምህርት ባለሙያዎችን፣ ለኮሌጅ እና ለሙያ የሚያቅዱ ተማሪዎችን፣ እና እንዲሁም የትምህርት ቤት መሪዎቻችን 51,000+ ተማሪዎቻችን የሚወደዱ መሆናቸውን የሚሰማቸው፣ ተፈታታኝ ሁኔታዎች የሚገጥማቸው፣ ማኅበረሰቦችን የሚገነቡ እና ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎች፣ ጋር እገናኛለሁ። ትምህርት ቤቶቻችን የሚያደርጓቸውን የእድገት ጉዞ እንዲቀጥሉ ለማድረግ፣ ተማሪዎችን ለስኬታማነት ለማብቃት የሚያስፈልጓቸውን የትምህርት አቅርቦቶች እንዲኖራቸው ማድረግ እንዳለብን ዐውቃለሁ።

በአለፈው ዓመት፣ ከማኅበረሰባችን ጋር በሥራ ተሰማርቼ በነበረበት ወቅት፣ የዲሲፒኤስ በጀት **ግልጽነት እና ተመጣጣኝነት** ያለው እንዲሆን ማድረግ ስላለው ጠቃሚነት፡ የሰጣችኋቸውን ገንቢ ሀሳቦቻችሁን አዳምጫለሁ። ያለ ግልጽነት አመኔታን ልንገነባ እንደማንችል እና ተመጣጣኝነት እና **ተማሪዎችን ከሁሉ በፊት ማስቀደም የበጀታችን አወሳሰን ዋና ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ** ዐውቃለሁ። በዲስትሪክቱ በመላ እየተካሄደ ያለው 2019-2020 የትምህርት ዓመት፣ ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት እና ከዚያም ባሻገር ላለው በጀት እቅዳችንን እየነደፍን ነው።

ለዚህ ግብ፣ ዲስትሪክቱ በበጀት ሂደት አኳያ፣ ሁለት ዋና እርምጃዎችን እየወሰደ ነው።

- **ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት፣ በ 2021 የበጀት ዓመት ሂሳብ የተመደበለትን የበጀት አደላደል ሂደትን ቤተሰቦቻችን እና ማኅበረሰቦቻችን ብሮቻችን በትምህርት ቤቶቻችን በመላ እንዴት እንደሚደለደሉ** ስለ ማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት በጀትም የበለጠ ሆኔታ እንዲረዱ ለማድረግ፣ **ይበልጥ አንጸባራቂ እንዲሆን ዲሲፒኤስ በቁርጠኛነት እየሠራ ነው።** ለ FY21 በጀት፣ ዲሲፒኤስ በተማሪ በጀት ገለጻ ላይ፣ የሕዝበ በጀት ማብራሪያ፣ እንዲሁም የክልል ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን (LSAT) በክብ ጠረጴዛዎች ውይይቶች አማካኝነት፣ ዲሲፒኤስ ከማኅበረሰቦቻችን ጋር ገንዘባችንን እንዴት እንደምናደላድል የየማኅበረሰባችን ፍላጎቶች ተንጸባርቀው እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን በዚህ መመሪያ፣ በተወሰነ ትምህርት ቤት የበጀት ከፍ እና ዝቅ የማለት መለዋወጥን ለመግለጽ የቃል ማብራሪያዎችን ጨምሮ የበጀት ሂደቱን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ስለምንወስዳቸው እርምጃዎች ለእናንተ እያብራራን ነው።
- **ለ 2022 የበጀት ዓመት በ 2021-2022, የትምህርት ዓመት ተግባራዊ የሚሆነውን የበጀት ሞዴላችንን በመላ እየገመገምን ሲሆን፣** የተማሪን የትምህርት ውጤቶች ለማሻሻል **እንዲችሉ የበጀት ሞዴላችንን እና የአሥራር ሂደታችን** ከሁሉ ይበልጥ በላቀ ሁኔታ አንጸባራቂነት ባለው ለሁሉም በእኩልነት በሚያደላድል እና አስተማማኝነት ባለው የገንዘብ በጄት የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን እንዴት እጅግ በላቀ ሁኔታ እንደሚሳተፉ ለመወሰን ነው። ከእኛዎቹ ዝንባሌ እና ፍላጎት ካላቸው እና ከእኛ ጋር ተሳትፎ ካላቸው አካላት እና እንዲሁም ከትምህርት ቤት በጀት ጠበብት ባለሙያዎች ጋር፣ በጄቶቻችን፣ ትምህርት ቤቶቻችችንን የሚያገለግሉ የተማሪዎችን እና የወላጆችን ፍላጎቶች የሚያሚሉ እንዲሆኑ እውን ለማድረግ በዚህ ሂደት እጅግ ወሳኝ ይሆናል። ይህ የክንውን ተሳትፎ በፀደይ 2020 ውስጥ ይካሄዳል።

ከትምህርት ቤቶች፣ ቤተሰቦች፣ እና ከማኅበረሰባችን ጋር አብረን አንድ ላይ በቅንጅት በመሥራት፣ የዲሲፒኤስ በጀትን ለሁሉም እንገነባለን። ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን እና ማኅበረሰብን ለስኬታማነት ለማብቃት የሚያስፈልገውን ሪሶርስ ማቅረብ እንድንችል ከእናንተ ጋር አብረን ለመሥራት በጉጉት እጠብቃለሁ።

በቅንጅት፣

Lewis D. Ferebee, Ed.D.
Chancellor
DC Public Schools



# የበጀት ክንውን የጊዜ ቅደም ተከተል

| | |
|---|---|
| ነሀሴ | የትምህርት ዓመት ይጀመራል። |
| ጥቅምት | የበጀት ዓመት ይጀመራል። |
| | የማኅበረሰብ መድረኮችን እና የሕዝብ በጉባዔ የበጀት ጉዳዮችን ቃል መስጫ መድረኮችን ጨምሮ እና የሕዝብ አስተዋጽዖ ማቅረቢያ ይጀመር እና ለሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ይቀጥላል። |
| ከጥር እስከ መጋቢት | ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት የታቀደ የተማሪዎች ምዝገባ ቆጠራ የዲስትሪክቱን የገንዘብ ምደባ መጠን ለመወሰን ይውላል። |
| | ዲሲፒኤስ ለቀጠዩ የትምህርት ዓመት መነሻ በጀት ለትምህርት ቤቶች ያቀርባል። |
| | LSATs ስለ ትምህርት ቤታቸው የታቀደ በጀት ውይይት ያደርጋሉ። |
| | ትምህርት ቤቶች የቀጣዩን ዓመት በጀት ያቀርባሉ። |
| | ዲሲፒኤስ የቀጣዩን ዓመት በጀት ያቀርባል። |
| ፀደይ | የዲሲ መማክርት ጉባዔ የቀጣዩን ዓመት በጀት ያፀድቃል። |
| ሰኔ/ሀምሌ | የትምህርት ዓመት ያበቃል። |
| በጋ | የዲስትሪክት መሪዎች የቀጣዩን ዓመት በጀት ለማፀደቅ ለጠቅላላ ብሄራዊ ሸንጎ ያቀርባሉ። |
| ነሀሴ | የትምህርት ዓመት ይጀመራል። |
| ጥቅምት | የበጀት ዓመት ይጀመራል። |

## **ግልጽ የመሆን ቁርጠኞነቶች** (TransparencyCommitments)

ዲሲፒኤስ በበጀት ሂደቱ እና ማኅበረሰባችን በጀት እንደሚደላደል እንዲገነዘቡ ለመርዳት እና ግልጽነትን ለማጎልበት በቁርጠኞነት ታጥቆ የቆመ ነው። ለበጀት ዓመት FY21፣ ዲሲፒኤስ፤

- **አዲስ የበጀት መረጃ ጎልቶ እንዲታይ ማድረግ።** በዲሲፒኤስ የመረጃ ማዕከል **ሳይት** www.dcpsdatacenter.com ድረ ገጽ ላይ አዲስ ሪሶርሶች፣ የማኅበረሰብ አባላት ትምህርት ቤቶች የግል ትምህርት ቤት ማኅበረሰቦችን ፍላጎቶች እንዲያንጸባርቅ በጀቶቻቸውንም ለየግላቸው እንዲያመቻቹት ለማስገንዘብ ይረዳል።

- **የትምህርት ቤት በጀቶችን በፈንድ መመደብ።** በፈንድ ምንጭ መመደብ (ለምሳሌ የክልል ፈንዶች፣ የበጎ አድራጎት ችሮታም ፈንዶች) ትምህርት ቤቶች የችሮታ ፈንዶቻቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱት የሚረዳቸው ይሆናል።

- **ከዓመት ወደ ዓመት የትምህርት ቤት በጀት ለውጦችን ማጠቃለል።** በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት መነሻ በጀት ድልድል ላይም የውይይት ክፍል ዋና ምዝገባ፣ የተወሰኑ ትምህርት ቤቶችን የመጀመሪያ ቀዳሚ ምደባ ላይ ጫና የሚያስከትል፣ ማናቸውንም ዋና ምዝገባ፣ም የተማሪ የማንነት መረጃ፣ ወይንም ፕሮግራም ቅያሬ ለውጦች ላይ ጫና የሚያሳድሩ ናቸው።

- **የትምህርት ቤት የበጀት መመሪያ የማጣሪያ ምርመራ።** መመሪያውን ግልጽ እና ይበልጥ ከእንከን የጸዳ እንዲሆን ማድረግን በሚም መለከት ለውጦች በማኅበረሰቡ ይነገራሉ። ለምሳሌ፣ የመረጃው ጽሑፍ ይበልጥ ሊገኝ የሚችል እንዲሆን ለማድረግ ዲሲፒኤስ፣ የሥራም አስፈጻሚ አካላት ማጠቃለያ ሊያክል ይችላል።

- **በማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት በጀት ላይ የበለጡ ይዘቶችን ሌሎች እንዲያውቋቸው ማድረግ።** በዚህ ዓመት፣ ይህ መመሪያ ስለም ማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት ተግባር፣ ስለ አጠቃላይ በጀቱ፣ እና ፈንዶችም እንዴት ወጪ እንደሚሆኑ ዝርዝሮችን ያቀርባል።



# ዲሲፒኤስእንዴትገንዘብእንደሚሞዱበለት ለት

## የገንዝብ ምደባ ምንጭ

በመሠረቱ ዲሲፒኤስ ፈንዲንግ ከክልል ከአካባቢ የታክስ ብሮች ፈንድ ይቀበላል። ዲሲፒኤስ በተጨማሪ ከ Title I and Head Start; ን ጨምሮ ከፌድራል የበጎ አአድራጎት ፈንድ የሚወሰድ ሲሆን፣ ለሕንጻዎች ጽዳት መጠበቂያ ከሚከፈል ክፍያ የሚገኝ ገቢን እና ከሕንጻዎች ኪራይ ገቢን ጨምሮ እና እንዲሁም እንደ ሌሎች ለሰው ልጅ ፍቅር የሚደረግ የገንዘብ ድጎማ (philanthropy); እና የልዩ አገልግሎት ቀረጥ እና ሌሎችንም የገቢ ምንጮች ጭምር ያካትታል።

።


### ጉዳዩ ቀጥታ ለሚመለከታቸው የበጀት እድሎች።

በየዓመቱ፣ ስለ በጀት በሚደረግ የተማሪዎች ክርክር ላይ እንዲሳተፉ ዲሲፒኤስ ከእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን ተወካዮች ይጋብዛል። እያንዳንዱ ተማሪ በዲሲፒኤስ የልማት መዋዕለ ነዋይ ፈሰስ ላይ ስለሚሰማው ስሜት ሀሳብ በማቅረብ በየትምህርት ቤታቸው ምን ማየት እንደሚፈልጉ ለምሳሌ ትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት፣ ቴክኖሎጂ፣ መሠረተ ዕውቀት፣ ማኅበራዊ ስሜታዊ ትም ህርት፣ እና ስለ ሌሎችንም  በሚመለከት የመፍትሄ ሀሳቦችን ይሰነዝራ።



በመጸው፣ የዲሲፒኤስ ቻንስለር እና አንጋፋ አመራሮች ከዋና ከዲሲፔስ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በመጭው የበጀት ዓመት ለማየት ስለሚፈ ልጓቸው ጉዳዮች ለመወያየት ዓመታዊ የሕዝብ የበጀት ክርክር ስብሰባ ጉባዔ ያካሂዳሉ። ዲሲፒኤስ በተጨማሪ ማኅበረሰቡ ይበልጥ ስለበጀት ሂደት እና ስለመጪው የበጀት ዓመት ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው ጉዳዮች እንዲያውቅ እና ከዲስትሪክት መሪዎች እና ቀጥታ ጉዳዩ ከሚያገባቸው ጓዶች ጋር በመወያየት ትምህርት እንዲያገኝ ዲሲፒኤስ የጋራ የመወያያ መድረክ ያካሂዳል።  ይህ በመጸው እና በክረምት ወቅት በማኅበረሰብ መድረኮች ይከናወናል።

## የዲስትሪክት ጠቅላላ ፈንዲግ (የበጀት ዓመት 2020)




## የክልል ፈንዲንግ

የዲሲፒኤስ የክልል ፈንዲንግ የሚወሰነው ወጥነት ባለው በተማሪ የንፍስ ወክፍ ቀመር አማካይነት (uniform per Student Funding Formula (UPSFF)) ስሌት ነው። ይህ ቅመራ ለእያንዳንዱ ተማሪ "በመሠረታዊ ደረጃ ("foundation level") እና በመሠረታዊ ደረጃም ላይ በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ተማሪ ሁኔታዎች ተጨማሪ ድጋፍ ያደርጋል።

ተጨማሪ ፈንድ፣ በተለየ የክፍል ደረጃዎች ለሚማሩ፣ የሆነ እክል ላለባቸው፣ የንጊሊዘኛ ቋንቋ ለሚማሩ፣ እና በ Opportunity Academies ለሚማሩ ተማሪዎች ይመደባል። ከእነዚህም ሌላ፣ ቤት የለሽ ተማሪዎችን፣ በማደጎ ይዞታ ሥር ለሚገኙ፣ ለችግረኛ ቤተሰቦች ለሚሰጥ ጊዜያዊ ድጋፍ (TANF) ፕሮግራም ወይንም ተጨማሪ የአልሚ ምግብ ፕሮግራም፣ እና እድሜአቸው ለተመ ዘገቡበት የክፍል ደረጃ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የሚሰጡ ድጋፎችን ጨምሮ ተጨማሪ ፈንድ የሚመደብላቸውን "ለአደጋ የተጋለጡ" ("at risk"] የሚለውን መገለጫ ለሚያሟሉ ተማሪዎች ተጨማሪ ፈንድ ይሰጣል።


ዲሲፒኤስ የሚያገኘውን ጠቅላላ የክልል የተማሪ የነፍስ ወከፍ ፈንዲንግ መጠን ለመወሰን ጠቅላላ የተማሪ የነፍስ ወከፍ ወጪ ተመን መጠን በመጠበቅ በዲሲፒኤስ ተመዝጋቢ ተማሪዎች ቁጥር በማባዛት የሚገኝ ነው። ለሁሉም ወጥ ለሆነ ለተማሪ የነፍስ ወከፍ ፈንዲንግ ቀመር የበለጠ መረጃ ለማግኘት code.dccouncil.us/dc/council/code/titles/38/chapters/29. ይቃኙ።

## ፌድራል ፈንዲንግ (Federal Funding)

ዲሲፒኤስ፣ ቀመርን ጨምሮ (ወይንም በምዝገባ ላይ የተመሠረተ) ፈንዲንግ እና ተወዳዳሪ የበጎ አድራጎት ፈንዲንግ በርካታ ልዩ ልዩ ዐይነት ፌድራል ፈንዲንግ ያገኛል። ይህም፣ ዝቅተኛ የገቢ መጠን ያላቸው ቤተሰቦች (Title I)፣ እክል ያለባቸውን ተማሪዎች (IDEA)፣ እና የእንጊሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎችን (Title III) ያካትታል።

## የዲስትሪክት ፈንዲንግ ሲዘረዘር (District Funding Breakdown)

ዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ ብልጫ ያላቸውን ፈንዶች ለትምህርት ቤቶች ያውላል። በበጀት ዓመት (Fiscal Year) 2020, ከበጀት ውስጥ ለእያንዳንዱ ብር፣ በይበልጥ 97 ሣንቲም የሚሆን ለትምህርት ቤቶች እንዲውል የተመደበ ወይንም ቀጥታ ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ የዋለ ነው።





# የትምህርት ቤት በጀቶች እንዴት እንደሚፈጠሩ

ትምህርት ቤቶች በጀቶቻቸውን ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት በሦስት የደረጃዎች ሂደት ያዘጋጃሉ።

## እርምጃ 1: ምዝገባ

የትምህርት ቤት በጀቶች ለመጭው የትምህርት ዓመት በሚጠበቅ የተመዝጋቢዎች ተማሪዎች ቁጥር መጠን ላይ ይመሠረታሉ። በየዘመኑ የተማሪዎች አመዘጋገብ ቁጥር መጠን መረጃ፣ የአካሄዱ አዝማሚያ፣ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከታሳቢነት በመውሰድ የሚወሰን ነው። የትምህርት ቤት በጀትን የማደራጀት ሂደቱን ለመጀመር፣ የዲፒኤስ ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ያልተጠበቀ የተመዝጋቢ የተማሪ ቁጥር ምን ያህል እንደነበረ በማየት ይወሰናል። ይህም በክፍል ደረጃ የተገመቱ የተማሪዎች ብዛትን፣ የሆነ እክል ያለባቸውን ተማሪዎች፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎችን፣ እና ለቅናሽ ዋጋ ምሳ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎችን ያካትታል።


## እርምጃ 2: መነሻ የገንዘብ ምደባ መጠን (Initial Funding Amount)

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት አገልግሎት እንደሚሰጠው ልዩ የተማሪዎች ሁኔታ መነሻ የፈንዲንግ መጠን፣ ወይንም ምደባ ይደርሰዋል። ይህ መነሻ ፈንዲንግ መጠን ከዚህ በታች ባሉት ሁኔታዎች መሠረት ይወሰናል።

- የሠራተኛ እና የመምህራን ሁለ አቀፍ ሞዴል። የሠራተኛ እና የመምህራን ሁለ አቀፍ ሞዴል (CSM) በሁሉም ቀጠናዎች የሚገኙ ተማሪዎች ሁሉ ከፍተኛ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት ገጠመኝ የሚያገኙ መሆናቸውን እርግጠኛ ለማድረግ፣ ትም ህርት ቤቶች ሁሉ በቂ የሥራ ደረጃዎች እና ተጨማሪ ፈንዲንግ እንዲኖራቸው ለማድረግ የተቀየሰ ነው። ለበለጠ መረጃ፣ dcpsdatacenter.com. ይቃኙ።

- መደበኛ ሠራተኛ ላልሆነ የሚመደብ ወጪ (Non-Personnel): እያንዳንዱ ትምህርት ቤት መደበኛ ሠራተኞች ላልሆኑ እንደ ለቴክኖሎጂ እና ለቁሳቁሶች የሚውል መዋዕለ ነዋይ ይመደበታል። መደበኛ ሠራተኞች ላልሆኑ የሚመደብ የፈንዲንግ መጠን የሚወሰነው በተማሪ የነፍስ ወከፍ ቀመር መሠረት ነው።

- ተጨማሪ ፈንዶች፤ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለበጎ አድራጎት ችሮታ በማመልከት ወይንም የዲስትሪክት የልዩ እቅድ እና ፕሮ ግራም፣ አካል በመሆን በተጨማሪ ፈንዲንግ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ UPSFF "ለአደጋ የተጋለጡ" ("at-risk.") የተሰኘውን ማብራሪያ የሚያሟሉ ተማሪዎች፣ ያሏቸው ትምህርት ቤቶች እነዚህን ተማሪዎች ለመደገፍ ተጨማሪ የሥራ መደብ ደረጃዎች እና ሪሶርሶች ሊያገኙ ይችላሉ።





አጠቃላይ ሁለ አቀፍ የሠራተኛ ምደባ ሞዴል (CSM) የትምህርት ቤት አመራርን (ለምሳሌ እንደ ርእሠ መምህር)፣ ለመምህርነት የሥራ መደብ (ለምሳሌ እንደ 1ደኛ ክፍል መምህር)፣ እና ሌሎችም የትምህርት ቤት ሠራተኞች (እንደ ሥነልቦና ባለሙያ መምህር፣ የትምህርት ቤት ሕንጻ ንጽሕና ጠባቂ፣ ወይንም ጋይዳንስ ካውንስለር (guidance counselor)፣ ጭምር ለመሳሰሉ ለትምህ ርት ቤት የሥራ ምድቦች ፈንድ ይመደባል። ሞዴሉ በተጨማሪ፣ አንዳንድ እክል ላለባቸው እና ለእንጊሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድጋፍ ለማድረግ ልዩ ጥረት ለሚያሳዩ ታታሪ መምህራን ፈንዲንግ ያቀርባል።

አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ እና የትምህርት ቅጥር ግቢዎች እያንዳንዳቸው፣ የተለያዩ የመምህራን እና የሠራተኞች ምደባ ሞዴሎች አሏቸው። ለም ሳሌ፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ርእሠ መምህር የሚመደብለት ሲሆን፣ ነግር ግን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአቴሌቲክ እና ለሥራ ክንውኖች ፈንዲንግ የሚያገኝ ሲሆን ፣ አንደኛ ደረጃ ትም ህርት ቤት ግን ለቅድመ መዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ረዳት ሠራተኛ በጀት ሊመደብለት ይችላል። በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ዐይነት ሞዴል የእያንዳንዱን ክፍል ልዩ መምህር ለተማሪ ጥመርታ ከሚያስፈልገው መሟላት ከሚገባው ጋር ከግምት ወይንም ከግንዛቤ ይወስዳል።

CSM ለመምህራን እና ለሠራተኞች ለሥራ መደቦች ፈንዲንግ የሚመደብ ሲሆን፣ ትምህርት ቤቶች በ CSM ላይ ለተመለከተው ለእያንዳንዱ ምድብ ቦታ ፈንዲንግ እንዲያውሉ አይጠበቅም። አንዳ ንድ ምድብ ቦታዎች፣ እንደ ርእሠ መምህር፣ ያሉ የግድ አስፈላጊዎች ናቸው። ሌሎች ቦታዎች እንደ ሁኔታ የሚወሰኑ ወይንም ትምህርት ቤት ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበውን ፈንዲንግ በተለየ ሁኔታ ላይ ማዋል እንዲችል ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል።

ስለ አጠቃላይ ሁለ አቀፍ የሠራተኞች አመዳደብ ሞዴል፣ የበለጠ መረጃ በ dcpsdataceter.com. ላይ ይገኛል።

## እርምጃ 3: የትምህርት ቤት በጀት መንደፍ (School Budget Development)

በጥር (January) እና የካቲት (February) መካከል፣ ርእሠ መምህራን፣ ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት በጀት ለመንደፍ የመጀመሪያ መነሻ በጀታቸውን መጠን ይጠቀሙበታል። ይህ ሂደት ከዚህ በታች የመለከቱትን እርምጃዎች ያካትታል።

- ተሳትፎ (Engagement)፤ ርእሠ መምህራን፣ ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት በጀቶቻቸውን ለመንደፍ ከየትምህርት ቤቶቻቸው LSAT ጋር ይሠራሉ። ርእሠ መምህራን እና LSATs ከመምህራን እና እና ሠራተኞች፣ ከወላጆች፣ እና ማኅበረሰቦች ተጨማሪ የአስተያየት መረጃዎችን ያሰባስባሉ። በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ሁሉ በፈንዶች እንደ አመቻቸው ለመጠቀም እንዲችሉ እነዚህን የሚያሰባሰቡ መረጃዎች ከታሳቢነት ሊወስዱ ይችላሉ።

- አስፈላጊ ለሆኑ የሥራ መደቦች በጀት መደልደል። ትምህርት ቤቶች በበጀቶቻቸው ላይ የተወሰኑ የሥራ መደቦችን እንዲያካትቱ ይጠበቃል። ለዚህ የሚሆኑ ምሳሌዎችም ርእሠ መምህራንን እና መምህራንን ይጨምራሉ።

- አመቺነት ላለው አወሳሰን የበጀት አደላደል፣(Budgeting for Flexible Decisions)፤ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎቻቸውን የትምህርት ስኬታማነት የሚረዳ ፕሮግራም ለመቀየስ፣ የሰው ኃይል ምደባ እና የበጀት ድልድል ውሳኔዎች ያደርጋሉ። በ CSM ሥር አመቺነት ያላቸው ለመምህራን እና ሠራተኞች የሥራ መደቦች፣ ትምህርት ቤቶች ከግቦቻቸው ጋር የሚጣጣሙ በተለያዩ ወጭዎች ላይ የተመደቡላቸውን ፈንዶች ሥራ ላይ ለማዋል፣ ትምህርት ቤቶች ከዲሲፒኤስ ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት ፈቃድ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ እንደ ከትምህርት በኋላ ፕሮግራም አቅራቢዎች ወይንም ለመምህራን እና ሠራተኞች ተጨማሪ የሙያ ማዳበሪያዎች ላይ በጀት ማዋልን ሊመስል ይችላል።

## እርምጃ 4: በጀትን የማጣራት በዲሲ የመማክርት ጉባዔ የማጽደቅ ተግባር።

**(Budget Reviewand Approval by DC Council)**

ያቀዷቸውን በጀቶች ርእሠ መምህራን ካቀረቡ በኋላ፣ ዲስፒኤስ የትምህርት ቤቶችን እና የማዕከላዊ ጽሕፈት ቤትን ጨምሮ፣ የታቀደውን የዲስትሪክቱን በጀት በማጠናቀር ለከንቲባዋ ያቀርባል። ከንተባዋም፣ የዲሲፒኤስን ከታቀዱ የዲሲ አስተዳደር መንግሥት በጀት ጋር በማከል ለማጸደቅ ለዲሲ የመማክርት ጉበዔ ያቀርባል።

የዲሲ መማክርት ጉባዔም በዲሲፒኤስ በጀት ላይ የክርክር ውይይት በማካሄድ፣ አስፈላጊ ለውጦችን እና ወይንም ተጨማሪዎችን በማከል የዲስትሪክቱን በጀት በመጨረሻ ያፀድቃል።

ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በጀት መረጃ በ dcpsdatacenter.com. ላይ ይገኛል።

የክልል ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን (LSAT) ለእያንዳንዱ የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት የቆሙ የተመርጡ እና የተሰየሙ አባላት ቡድን ናቸው። ቡድኑ፣ ወላጆችን፣ መምህራንን፣ ሌሎች ከማስተማር ሥራ የተለዩ ሠራተኞችን፣ በአንዳንድ የተወሰኑ ሁኔታዎችም ተማሪዎችን ይይዛል። ይህ ቡድን የትምህርት ቤቱን በጀት መንደፍን ጨምሮ፣ ለተማሪዎች ሁሉ የሚጠበቁ ከፍተኛ ውጤቶችን የመቀዳጀት ጉደዮችን በሚያራምዱ ሁኔታዎች ላይ ርእሠ መምህርን የሚያማክር ነው።





### የዲሲፒኤስ አማካይ ደሞዝ (Average Salaries at DCPS)

የዲሲፒኤስ በጀት ልትምህርት ቤት ሁሉ የተመሠረተ ለትምህርት ቤት መምህራን እና ሠራተኞች በጀት፣ አማካይ ወጪ ነው። በዚህ መሠረት፣ እያንዳንዱ የሥራ መደብ፣ ደሞዝን እና ጥቅማ ጥቅሞችን እና የትምርሀት ቤቱንም የበጀት መንድፍ አማካይ ወጪ ጨምሮ፡ ትምህርት ቤት፣ ለእያንዳንዱ የመምህርነት እና የሌሎች ሠራተኞች የሥራ መደብ አማካይ የክፍያ ሂሳብ ፈንዲንግ ይደርሰዋል። የትምህርት ቤት ቅጥር መምህር ሠራተኛ አባል፣ ከፍም ይሁን ዝቀ አለ ከአማካዩ የደሞዝ ክፍያ ያገኛል” በመህራን እና ሠራተኞች መለዋወጥ ምክንያት በአማካይ በደሞዝ ክፍያዎች ሂሳብ መጠቀም ትምህርት ቤቶች ከፍ እና ዝቅ ከሚል የቅጥር ደሞዝ ሂሳብ ውጣውረድ የአከፋፈል ጣጣ የሚጠበቅባቸው ከመሆኑም ባሻገር መምህራኣበጥራት ለመቅጠር የሚያስላቸው ይሆናል።




# ማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት በጀት እንዴት እንደሚመደብለት

ዲሲፒኤስ በትምህርት ቤት የተማሪዎችን ስኬታማነትን ለማጎልበት ሪሶርሶችን በትምህርት ቤት ተግባላር ላይ ለማዋል በቁርጠኛነት የቆመ ነው። በአጠቃላይ በመምህራን እና በሠራተኞች ምደባ ሞዴል እና በማዕከላዊው አገልግሎት ትምህርት ቤቶችን መርዳት፣ በዚህም ግብ ላይ በመመ ሥረት፣ በርካታ ፈንዶችን በትምህርት ቤት ሥራ ላይ እናውላለን።

የማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት ተግባር፣ በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ እኩልነትን ማራመድ፣ እጅግ ለከፍተኛ በጣም ጥሩነት ግልጽ መስፈርቶችን ማቆም፣ እና እንዲሁም ትምህርት ቤቶች እነዚህን የመጠበቁ ሁኔታዎችን እንዲያሳኩ መርዳት ነው። የዲሲፒኤስ ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት በጀት በእንዲህ ዐይነቶች የማዋዕለ ነዋይ (investments) ተግባር ላይ በማዋል ትምህርት ቤቶችን ይደግፋል።

- **የትምህርት ቤት መሠረት ያላቸው የሥራ መደቦች (School-based positions)፤** እነዚህ የማዕከላዊ በጀት ድልድል መደ ቦች፣ የማኅበራዊ አገልግሎት ሠራተኞችን እና የሥነ ልቦና ባለሙያዎችን ጨምሮ እንደ የምግብ አገልግሎቶችን፣ አቴሌቶችን፣ እና እክል ላለባ ቸው ተማሪዎች ተዛማጅ አቅርቦት አገልግሎቶች ለመሳሰሉ ድጋፍ ይሰጣሉ።

- **የትምህርት ቤት ድጋፍ (School support)፤** እነዚህ ምደባዎች፣ ሥርዓተ ትምህርትን እና ትምህርት አሰጣጥን፣ አስተ ዳደርን፣ እና የቴክኒክ ድጋፍን (ለምሳሌ፣ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ስብስብ ድጋፍ የሚሰጡ) ለመሳሰሉ እርዳታ ያደርጋሉ።

- **ማዕከላዊ አስተዳደር (Central administration)፤** እነዚህ ምደባዎች፣ የግዥ አቅርቦቶችን (procurement)፣ ሰብአዊ ሪሶርሶችን፣ እና የፋይናንስ አስተዳደርን ለመሳሰሉ የዲስትሪክቱ ተግባራት ድጋፍ ያበረክታሉ።

ለተወሰኑ ፐርሶኔል (personnel)፣ ንብረቶች እና አገልግሎቶች ማዕከላዊ በጀት በመመደብ፣ ዲሲፒኤስ፣ አንስ ባለ ወጪ ከፍ ያለ የሥራ ውጤትን፣ በንብረት አገዛዝ አቅርቦት ብቃትን በመቀዳጀት፣ በመላ እና በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ቁጥር ከፍ እና ዝቅ ከማለት ጋር የበጀት ማጣጣምን ደንብ ዲሲፒኤስ ይጠብቃል።

## የበጀት ዓመት 20 ትምህርት ቤቶች እና ማዕከላ የበጀት ድልድል
## (FY20 Schools and Central Allocations)

የበጀት ዓመት FY20 ዐሥረኛው የተከታታይ ዓመታት የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክት በጀት የትምህርት ቤቶችን ፈንዲንግ ከፍ እንዲል እድርጓል። በበጀት አመዳደብ ሂደት፣ ዲሲፒኤስ ምንጊዜም ለትምህርት ቤት ቅርበት ላላቸው ጉዳዮች ቅድሚያ ይሰ ጣል። ከበጀት ዓመት FY15 ጀምሮ፣ ዲሲፒኤስ ለማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት አስተዳደር ወጪ በጄት አጠቃላይ ከብር አንጻር ሲታይ አንዳ ችም ሳይጨምር በነበረበት ሲጓዝ ቆይቷል። ለበጀት ዓመት FY20፣ ዲሲፒኤስ የሚከተሉትን ወጭ አድርጓል።

- $874.9 ሚሊዮን፣ ወይንም በትምህርት ቤት እና የትምህርት ቤት መሠረት ላላቸው ተግባራት ድጋፍ የሚሆን 84% የሚያህል አውሏል።[1]
- $144.6 ሚሊዮን፣ ወይንም 13% ለትምህርት ቤት ድጋፍ የሚውል የሥራ ማስኬጃ በጀት።
- $32.1 ሚሊዮን፣ ወይንም 3% የሥራ ማስኬጃ በጀቱን ለማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት እስተዳደር አገልግሎት ተግባር መድቧል።

የዲሲፒኤስ ጠቅላላ በጀት፣ የማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት በጄት፣ የፌድራል እና ሌሎች የበጎ አድራጎት ችሮታዎችን የመሳሰሉ አካባቢና አካባቢ ካልሆኑ ፈንዶች የሚውጣጣ ነው። ዲሲፒኤስ በየዓመቱ የበጀት ደንቦቹን ከዋናው የፋይናንስ ጽሕፈት ቤት (OCFO) ጋር በመሆን እየመረመረ ያጣራል።

## ጉልህ ማዕከላዊ ድልድል (Significant Central Allocations)

ይህ ክፍል በማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት የሚካሄዱ በርካታ፣ በጉልህ የታቀዱ ዲሲፒኤስ ለትምህርት ዓመት FY20 ለትምህርት ቤቶች የሚሰጣቸውን ይዘረዝራል።

- **የምግብ አገልግሎቶች፤** ተማሪዎች ጤናማ ምግቦችን የሚያገኙ መሆናቸውን ዕውን ለማድረግ ለትምህርት የአልሚ ምግብ ፕሮግራም ማካሄጃ የሚወል **$54 ሚሊዮን።**

- **ለሕንጻ እያያዝ (Building Maintenance:) $28 ሚሊዮን** የኤሌትሪክ፣ የጋዝ፣ እና የውኃ ወጭዎችን ጨምሮ ለትምህርት ቤት ግቢ ኢያያዝ ወጪዎች፣

- **የመረጃ ቴክኖሎጂ (Information Technology:) $25 ሚሊዮን** ለቴክኖሎጂ፣ የመረጃ ሥልቶች (data systems)፣ እና ለዲሲፒኤስ ተማሪዎች ለቴክኖሎጂ ድጋፍ፣ መምህራን እና ሠራተኞች።

- **ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች (Related service providers)፤ $19 ሚሊዮን** አንዳንድ እክል ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለሚያበረክቱ መምህራን እና ሠራተኞች ወጪ። ከብዙ በጥቂቱ የመስማት ችግር ላለባቸው የጆሮ ሀኪም ባለሙያዎች (audiologists)፣ አኩፔሽናል ቴራፒስትስ (occupational therapists)፣ ለፊዚካል ቴራፒስትስ (physical therapists)፣ የመናገር ችግር ላለባቸው ፓታሎጂስትስ (speechlanguage pathologists)፣ እና ስፒች ቴራ ፒስት (speech therapists)፣ ከብዙ በጥቂቱ ለመሳሰሉ ወጭ የሚውል በማዕከላዊነት የሚመራ ሲሆን፣ ለዚህም ምክንያቱ እነዚህ ባለሙያዎች እነዚህን ዐይነት የመሳሰሉ ችግሮች ያሉባቸውን ተማሪዎች በበርካታ ትምህርት ቤቶች ስለሚያገለግሉ ነው።

- **አቴሌቲክስ፤ (Athletics) $7 ሚሊዮን** ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድረስ የአቴሌቲክስ አገልግሎት ስለሚያበረክቱ ነው።

1 በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረተ የማዕከላዊ በጀት ምደባዎች በዚህ ቁጥር ውስጥ የተካተቱ ናቸው። የማዕከላዊ በጀት በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረተ ምደባ፣ እንደ አኩፔሽናል ቴራፒስት (Occupational Therapist) ዐይነት ሲሆን ፣ ይህም በርካታ ትምህርት ቤቶችን የሚያገለግል እና በሚቀርቡ የተማሪዎች ችግር ጥያቄ ብዛት መሠረት በሽፍት የሚንቀሳቀስ ነው።

## ማዕከላዊው በጀት እንዴት እንደሚነደፍ (How Central Budget is Developed)

በየዓመቱ፣ ዲሲፒኤስ የትምህርት ቤቶቻችንን በጀቶች ይጀምር እና ከዚያ በኋላ የማዕከላዊውን ጽሕፈት ቤት በጀት የመዘርጋት ተግባር ያካሂዳል። የማዕከላዊው ጽሕፈት ቤትን የበጀት አመዳደብ ለመወሰን፣ ዲሲፒኤስ በጥንቃቄ ማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን ድጋፍ በጥንቃቄ ይመረምራል። በተለይም ከዚህ ጋር በተያያዘ፤

- ዲሲፒኤስ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ስለሚገቡ ሰለ በጀት፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በመጻው ሀሳብ ለማግኘት ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ መድረክ ያካሂዳል። ለምሳሌ፣ ዲሲፒኤስ ዓመታዊ የሕዝብ የበጀት ውይይት፣ ዓመታዊ የተማሪዎች የበጀት ጉዳይ ውይይት መድረክ፣ እና ተጨማሪ የማኅበረሰብ የውይይት መድረኮች ያካሂዳል።
- የዲሲፒኤስ ሥራ ላይ ለማዋል የመደበው በጀት ግቦችን (Capital Commitment goals) መሪዎች መርምረው በማየት ከሥራ ዘርፎቻቸው ጋር እንዲጣጣም ያደርጋሉ።
- መሪዎች ህጋዊ እና በስምምነት የሚከናወኑ ትዕዛዞችን ከጽሕፈት ቤቶቻቸው ጋር የተዛመዱ (ለምሳሌ ጥቅማ ጥቆምችን የመሳሰሉ ለመኖሪያ የሚያስፈልጉ ሰብአዊ እርዳታ እና ድጋፍ አግልጎቶችን ማበርከት)።
- በትምህርት ቤቶች ላይ እና ለማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት ሥራ ማንቀሳቀሻ በሚውል በዲሲፒኤስ የታቀደ በጀት የሚወሰን ሲሆን፣ የማዕከላዊ ጽሕፈት ቤቱን በጀት ድልድል ይወስናል።

## የዲሲፒኤስ በጀት ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች እንዴት እንደሚለይ

(How DCPS' Budget Differs from Other School Districts)

ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች በጀት ጋር ሲወዳደር ልዩ የሚሆንባቸው በርካታ መንገዶች አሉ።

- የዲሲፒኤስ የታቀደ በጀት በከተማይቱ እቅድ በጀት ውስጥ ተካቷል። የከተማይቱ በጀት ለጠቅላላ ኮንግሬስ ጉባዔ ይቀርባል። የሌሎች ዲስትሪክቶች በጀቶች በትምህርት ቤቶቻቸው እማካይነት ሥራ ላይ የሚውል ነው።

- ዲሲፒኤስ፣ የፌድራል የበጀት ዓመትን (ከጥቅምት (ከጥቅምት (October) 1 እስከ መስከረም (September) 30) ይከተላል። ሊሎች በርካታ የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች የየራሳቸውን የበጀት ዓመት ይወስናሉ። (ከትምህርት ዓመቱ ጋር ተጣጥሞ ለመጓዝ አብዛኛውን ጊዜ ከሀምሌ (July) 1 እስከ ሰኔ (June) 30) ድረስ ይካሄዳሉ።

- ዲሲፒኤስ የክልል ፈንዶችን ከዓመት ወደ ዓመት ማሸጋገር አይችሉም። ሌሎች በርካታ የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ በቀጣይነት በሚካሄድው ሥልታዊ የተጣጣመ ጉዞ ለማድረግ ዲስትሪክቱን የሚያስችል የፈንዶች መጠባበቂያ ይኖራቸዋል።

- ዲሲፒኤስ እንደ ጥቂት የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች ከሌሎች ዲስቲሪክቶች ለየት ባለ ሁኔታ ትምህርት ቤቶችን ፈንድ ለማድረግ የንብረት ላይ የታክሶች ጫና ጭማሪ (levy taxes) አያደርግም።

- ዲሲፒኤስ የራሱን የሂሳብ ቻርት (ምሳሌ፣ በበጀት ውስጥ የሥራ ተግባሮችን)፣ የማይፈጥር ሲሆን፣ በዚህ ፋንታ የከተማዋን የሂሳብ ቻርት ይከተላል።

1. የገንዘብ ጽሕፈት ቤት ዋና ኃላፊ (OCFO)፣ ዲሲፒኤስን ጨምሮ፣ ለዲሲ አስተዳደር መንግሥት የገንዘብ እንቅስቃሴ ተግባራትን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል። የ OCFO ሠራተኞች የዲሲፒኤስ ሂሳብን ያስተዳድራሉ። በተጨማሪ፣ OCFO ዲሲፒኤስ እና ሌሎች የከተማይቱ ወኪሎች የሚጠቀሙበትን ከተማ አቀፍ የገንዘብ ሥልትን ይቆጣጠራል። ሌሎች የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች የየራሳቸውን የገንዘብ ሥልቶች ይቆጥጠራሉ፣ እናም ይመራሉ።

## የዲሲፒኤስ ካፒታል በጀት

ዲሲፒኤስ በየዓመቱ፣ በስምንቱም ክልሎች በሙሉ የ21ደኛው ክፍለ ዘመን የትምህርት ክልል የምናስተናግድ መሆናችንን ዕውን ለማድረግ ዲሲፒኤስ ካፒታል ፈንዶችን ይመድባል። ካፒታል በጀታችንን፣ በዲስሪክቱ ካፒታል የማሻሻያ እቅድ (CIP) እና ዘመናዊ የሆኑ ለትምህርት ቤቶች ሕንጻዎችን ለመቀየስ እና ለመገንባት፣ እንዲሁም በግንባታ ፕሮጄክቶች በትንሽ ካፒታል C.W. Harris አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ Houston አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ Jefferson መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ Eliot-Hine መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና በታሪካዊው Thaddeus Stevens ህንጻ ቀደም ያለ የመማሪያ ማዕከል ዘመናዊ እንዲሆኑ የማድረግ ፕሮጀችቶችን ለማጠናቀቅ የሚውል ነው።

## ጥያቄዎች?

ለበለጠ መረጃ፣ dcps.dc.gov/budget.ን ይቃኙ።

ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከ **51,000** በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን የሚያስተናግዱ **ሲሆን 117 ትምህርት ቤቶችን በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ያካሂዳሉ።**

